ክበር ይሳሉ ንገስ ይሳሉ
በምድር ያሉ በሰማይ ያሉ
ሲሉ ሰምቼ ጌታ ነህ አልኩኝ
እኔም ለራሴ ጌታዬ ነህ አልኩኝ
አዎ አመልክሃለሁ ጌታ አመልክሃለሁ

ዝም ብዬ ሳስብ ሳሰላስለው

እግዚአብሄር እንዴት ድንቅ ነው (2)

ምህረቱን አስቤ አሜን ስል ፍቅሩ አለ ለካ

ፍቅሩን አስቤ አሜን ስል ባርኮቱ አለ ለካ

አለ ለካ እረ እንዴት አመስግኜው ልርካ (2)

አልጠፋብህ አለኝ ከልቤ ውስጥ
የእግዚአብሂር ፍቅር
አሳዳጊነቱ አባትነቱ ከህይወቴ ጅምር
ትዝታ አይደለም ወይ እያነሳው ምተርክለት
በርሱ አይደለም ወይ እስካሁን ድረስ ያለሁት

የእግዚአብሄር ምህረት አቤት
እሩሩህነትህ አቤት
. የፍቅሩ ጥልቀት አቤት
ሰው ወዳድነት አቤት

አንድ ሁለት ብዬ ውለታውን አስቤ ልቆጥር
ጥፍት ይለኛል ከየት ተነስቼ እንደምጀምር
ይህ እንኳን ቢረዳኝ ቢነግርልኝ ውስጤን ቢገልጻው
እንደእግዚአብሄ ያለ የለም ብዬ ልደምደመው

እንደ እግዚአብሄር  የለም አቤት (3) ቢፈለግ ዘላለም
እንደርሱ የለም አቤት (3) ቢፈለግ ዘላለም አቤት (3)

ለኛስ በዝቶልን ነው እንጂ ምህረትህ ቸርነትህ
ፊትህ መቆማችን አይደለም በጽድቃችን

አንተ በዙፋንህ ላይ ነህ (2)
ጌታ ልገዛልህ ልኡል ልስገድልህ

ታሪኬን የለዋወጠው
ኑሮዬን እንዲህ ያስዋበከው
ኤልሻዳይ ለዘላለም ነህና
ይብዛልህ አህንም ምስጋና (3)

# መድሃኒቴ እግዚአብሄር ነው

ታዲያ ስሱ ምን እሳለሁ
ይህን ሁሉ ያደረገው
ታዲያ ስሱ ምን እሳለሁ
ምስጋናዬን አበዛለሁ
አልቻልኩም ዝም ልል አልቻልኩም (2)
ማዳኑ ይጎተጉተኛል ተነሳ (ሺ) አመስግን (ኚ) ይለኛል
ይህም ሳንተ ትንሽ ነው ያለኝን እሰጥሃለሁ

ዝም የማያሰኝ ብዙ ምክንያት አለን
እንዳመሰግንህ የሚጎተጉተኝ
አምላኬ ተባረክ ተወደስ ተቀደስ

አልቻልኩም ዝም ልል አልቻልኩም (2)
ማዳኑ ይጎተጉተኛል ተነሳ (ሺ) አመስግን (ኚ) ይለኛል
ይህም ላንተ ትንሽ ነው ያለኝን እሰጥሃለሁ
አምላኬ ተባረክ ተወደስ ተቀደስ
ይህም ላንተ ትንሽ ነው ያለኝን እሰጥሃለሁ